# አዲስ አበባንና አካባቢዋን ከኦሮሞ የማጽዳት አዋጅ

ሰርጸ ደስታ

June 29, 2017 20:50



እኔ ብዙ ጊዜ ብዬዋለሁ የዛሬውን ብዙ የኦሮሞ ትውልድ ወያኔ በራሱ ስለሰራችው እንደፈለገች እንደምትዘውረው ታውቃለች፡፡ ከወያኔ ጋር የኦሮሞን ሕዝብ ልጆች ለማምከን ብዙ በኦሮሞ ሥም የተንቀሳቀሱ ድርጅቶች አሉ፡፡ በዋናነት ግን ኦነግ ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳል፡፡ ቁጥሩ አነሰም በዛም ዛሬ ላይ ድምጹ ከፍ ብሎ የሚሰማው ይሄው ወያኔ የሰራችው ትውልድ ድምጽ ነው፡፡ መቼም ይህን ከሚያክል ሕዝብ የተወሰነም ቢሆን የሚያስተውል ይጠፋል ብዬ አላስብም፡፡

እነ መረራና የሱ አጋሮች ዛሬ ላይ መናገር አይችሉም፡፡ ግን ቢያንስ የእነ መረራን መርህ የሚከተል ትንሽም ቢሆን ይገባዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡ የኦሮሞ ሕዝብ ከመጀመሪያው ጀምሮ በዋናነት አማራ ከሚባለው ሕዝብ ጋር ልዩ ጥላቻ እንዲያድርበት በፖሊሲ ጭምር ታግዞ ሲሰራበት ነው የቆየው፡፡ ዛሬ ላለው ኦሮሞ እየገደለው ያለው ወያኔ ምኑም አደለ፡፡ ዋና ጠላት አድርጎ የሚያስበው የኦሮሞ ክብርና ልዕልና ከፍ ያለበትን የሚኒሊክ ታሪክ ነው፡፡ ይህን እውነት እስከሚገባው ድረስ ኦሮሞ ከክብር እየወረደ እንደሚሄድ አትጠራጠሩ፡፡ ኦሮሞ በኦሮሞ ሥም በሚኒሊክ ዘመን ያለው ታሪክ ሁሉ በውሸት የተቀናበረለት አኖሌ ብቻ ነው፡፡ ሲያስኙውም ጨለንቆን ይጨምራል፡፡ ልብ በሉ አሁን እየተነገረ ያለው የአኖሌ ታሪክ ፍፁም ውሸት ሲሆን በአርሲ የነበረው ጦርነት ግን ብዙ ጥፋት እንደነበረው የራሳቸው የሚኒሊክ መዋዕለ ዜናም መዝግቦት ይነበባል፡፡ ጨለንቆን ካሰባችሁ ከእነ ጭርሱም ከኦሮሞ ጋር የተደረገ ጦርነት አልነበረም፡፡ ከሀረሪው ገዥ ጋር ነበር እንጂ፡፡ ዛሬ ዘጠና ከመቶ በላይ የሚሆነው  ኦሮሞ ጨለንቆን ከኦሮሞ ጋር የተደረገ ጦርነት እንደሆነ ነው የሚያውቀው፡፡ ዛሬ የሚነገረው የአኖሌውንም የጨለንጦውንም የውሸት ታሪክ አስተውላችሁት እንደሆን እየተቀነቀነ ያለው በሙስሊም አክራሪዎች ነው፡፡ ኦሮሞን በሙሉ በሙስሊም አክራሪ ሴራ ውስጥ እየተጠቀሙበት ነው፡፡

በተቃራኒው ታላላቅ ዝናና ገድልን የፈጸሙ የኦሮሞ ጀግኖች ታሪክ እንዲዋረድ ተደርጓል፡፡ ጀግኖቹ በአብዛኛው ከክርስቲያን ኦሮሞ ስለነበሩ ይህን ሆን ተብሎ ነበር ዘመቻው የተካሄደው፡፡ ጀግኖቹን አለም ሳይቀር መዝግቧቸዋል የኦሮሞ ሕዝብ ግን የገዛ ጀግኖቹንና ታሪኩን አጥቶ ምልከት የሌለው የመከነና ተቅበዝባዥ ወኔው የከዳው ሆኗል፡፡ ጎበናን ያቃልላል ያልታወቀ የሰፈር ሽፍታ እያመጡ ጀግና ይሰይሙለታል፡፡ ገበየሁ ጎራን፣ ባልቻ ሳፎን፣ እና እልቆ መሳፍርት የኦሮሞ ጀግኖች በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ የሉም፡፡ እና ምን ባዶ ምልክት የሌለው ሕዝብ ምን ወኔና አቅም ይኖረዋል እንደፈለጉ ለሚዘውሩት ራሱን ሰጥቶ፡፡ ከዚህ ነበር የጀመረው የኦሮሞ ሕዝብ ውድቀት፡፡

በኃይለሥላሴም በደርግም ኦሮሞ እንደማኝኛውም ዜጋ የራሱ ድርሻ ነበረው፡፡ ይህ የኦሮሞ ትውልድ ግን ድርሻ አልነበረኝም ይላል፡፡ ዛሬ ግን አስተውሉ አሮሞ ምንም ውስጥ የለም፡፡ ሲስተማቲካል ሙልጭ ብሎ ከኢትዮጵያ ተሳትፎ ውስጥ ወጥቷል፡፡ ኦሮሞ በንግድ ውስጥ የለም፣ በስልጣን የለም፣ በትልልቅ ተቋማት የለም፣ ድሮ በሚታወቅበት በመከላከያ ሰራዊት መሪነት ውስጥ እንኳን ባዶ እንዲሆን ነው የተደረገው፡፡ ብልጦቹን የኦሮሞ ልጆች ሲስተማቲካሊ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት እንዳይኖራቸው ተደረገ፡፡ ኦሮሞን ዛሬ ብታዩት ምንም የለውም፡፡ ባለሀብት ጥሩ! ባለስልጣን ጥሩ! ኦሮሞ ምንም ውስጥ የለም፡፡ ኦሮሞ ኦሮሚያ የምትባል የቅዠት አገር ውስጥ ነው የሚኖረው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ዛሬ አሮሞ የለም፡፡ ይሄው ዛሬ 26 ዓመት አለፈው አሁንም አልነቃ ብሏል፡፡ ቋንቋ፣ ከተማ፣ የቦታ ሥያሜ ምናምን እያሉ ይደልሉታል፡፡ መሠረታዊ ማንነቱንና በአገሪቱ ያለውን ኢኮኖሚያዊም በሉት ማህበራዊና ፖለቲካዊ ድርሻ ግን እንዳይኖረው ተደርጎ ተጠርንፏል፡፡ ናዝሬት አዳማ፣ ደብረዘይት ቢሾፍቱ፣ ዝዋይ ባቱ፣ ተባሉ መልካም፡፡ ግን ለኦሮሞ

ምን ጠቀመው; ኦሮሞ በእንደነዚህ አይነት መደለያዎች እንደሚዘወር ስለተረዱት ታሪክም እውነትም መጠበቅ አያስፈልግም ብቻ ኦሮምኛ በማድረግ ኦሮሞን አፉን መዝጋት እንደሚቻል ሰዎቹ ተማምተናዋል፡፡ አዳማ በትክክልም ታሪካዊ ሥያሜዋን እንዳገኘች አልጠራጠርም መልካም ይህ ለኦሮሞ ሳይሆን ሌላውም ይጋራዋል፡፡ ዝዋይን ባቱ ብሎ መሠየም ግን ኦሮሞን ለመደለል ከተከደበትም አካሄድ በላይ ታሪካዊ ስህተትና የሌሎችን ታሪክ የሚጋፋ ነበር፡፡ ይህ ቦታ ከጥንት ጀምሮ ከዜይ ሕዝብ ጋር የተገናኘ ነው፡፡ ከኦሮሞም ሕዝብ በፊት የዜይ ሕዝብ በዚህ ቦታ ይኖር ነበር፡፡ ሀይቁ በእነዚሁ በዜይ ሕዝቦች ስም ዝዋይ ተባለ ከተማው ደግሞ ከሀይቁ ሥያሜውን አገኘ፡፡ ይህ ሁሉ እየሆነ ያለው በወያኔና ኦሮሞን ከኢትዮጵያዊነት ቦታ ድራሹን ያጠፉት በቅዠት አገር በሚያኖሩት ነው፡፡ ኦሮሞን የከበበው ሕዝብ ሁሉ ኦሮሚያ የምትባለው አገር እውን ብትሆን ኦሮሞ ዋና ጠላታቸው እንደሆነ ያውቃሉ፡፡ ለአለፉት 26 ዓመት የኦሮሞ ሕዝብ ያልተጋጨው አዋሳኝ የለም፡፡ ምክነያቱም በኦሮሞነት ሌላውን እንዲጠላ በመደረጉ ነው፡፡ እናም ዛሬ ኦሮሞ ሲባል የትኛውም ሕዝብ በበጎ አያይውም፡፡ እንደውም አማራ ከተባለው ጋር በተወሰነም ቢሆን መግባባቱ አለ፡፡

አሁን አዲስ አበባን ለኦሮሞ ጥቅም ማስከበር በሚል የተደረገው ይሄው ለዘመናት በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ሲቆመር የነበረው አሰራር ነው፡፡ ኦሮሞ በሌሎች ሕዝቦች እንዲጠላ ማድረግ የበለጠ ባዶ እንዲሆን የበለጠ እንዲምታታ ማድረግ፡፡ ኦሮሞ ከአልታገለ ወያኔ ብዙ እድሜ እንዳላት ታውቃለች፡፡ የወያኔ መጥፊያዋ ኦሮሞ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር የተባበረ ዕለት ነው፡፡ በወሳኝነት ቦታ እንዲሳተፍ አይፈለግም፡፡ ምክነያቱም በራስ መተማመን እንዳያመጣ፡፡ እንዲሁ የተወናበደ በራሱ የማይተማመን ኦሮሞ ነህ በሚል እየተደለለ እንዲኖር ነው በዋናነት እየተሰራበት ያለው፡፡ አስቂኙ የኦሮምን ጥቅም ያስጠብቃል የተባለው የአዲስ አባባ ከተማ አዋጅ ፍፁም ሕገ ወጥ ከመሆኑም በላይ ዳግም ኦሮሞን ከሌሎች ሕዝቦች ጋር ሕብረት እንዳይኖረው የሚያደርግ፣ ግን ምንም አይነት ትቅም እንዳይኖረው የተቀለፈበት ነው፡፡ በግልፅ ግን የኦሮሞ ገበሬዎች በስፋት እንደሚፈናቀሉ ደንግጓል፡፡ አላማውም መሬቱን ከኦሮሞ ማጽዳት ነው፡፡ ልብ በሉ ዛሬ ሰዎቹ ገንዘብ ስላላቸው መሬቱን ሊገዙት ይችላሉ፡፡ ለኦሮሞ ገበሬውም በቂ ገንዘብ ሊሰጡት ይችላሉ፡፡

በዚህ ሂደት አዲስ አበባና ዙሪያዋ ከኦሮሞ የጸዳች አካባቢ ይሆናል፡፡ ቀመሩ ይህ ነው፡፡

ለኦሮሞ ወጣቶች ሥራ እንሰጣለን የሚለው ሌላው አሳዛኝ ንቀት ነው፡፡ የኦሮሞ ወጣት የሀብት ባለቤት ሳይሆን የሚሆነው ተቀጣሪ ባሪያ ነው፡፡ ሀብቱ ውስጥ መቼም እድል እንዳይኖረው ሰርተውበታል፡፡ የእነሱን ፋብሪካዎችና ድርጅቶች ለማንቀሳቀስ ኦሮሞ ያስፈልጋል፡፡ ድሮስ የጉልበት ሠራተኛ የሚሆነው ማን ነው; ይህ አሳዛኙ ነገር አንዱ ነው፡፡ በአጠቃላይ ይህ አዋጅ ኦሮሞን በቀጣይም ከተሳትፎ በማራቅ በራስ መተማመኑን ሁሉ በማጥፋት የተገዥነት እውነታውን አሜን ብሎ እንዲቀበል የተደረገ ነው፡፡ አዲስ አበባን የሚሟገተው ኦሮሞ መላው ኦሮሚያ የተባለውን አገሩን ራሱ እንዳጣ አያውቅም፡፡ በዚህ አዋጅ ብዙዎች ጮቤ ረግጠዋል፡፡ ይህ ይጠበቅ ነበር፡፡ ይህንንም ታስቦ ነበር አዋጁ፡፡ አዋጁ የኦሮሞን ሕዝብ ዝም ለማሰኘት ታስቦ የወጣ እንጂ ወያኔ የደረሰችውን ሕገመንግስቷ አንቀጽ 49/5 የሚለው ጋር ምንም አይገናኝም፡፡ አዋጁ አዲስ አበባ በኦሮሚያ እምብርት ላይ በመሆኗ እያለ በተደጋጋሚ ይናገራል፡፡ ይህ ማሳከር ነበር፡፡

አንቀጽ ተብዬው የሚለው አዲስ አበባ በኦሮሚያ ክልል መሀል ስለሚገኝ ነው የሚለው፡፡ መሀል ማለት አካለ ነው ማለት አደለም፡፡ ራሱን የቻለ አስተዳደርም አለው፡፡ አዲስ አበባ የራሱ መስተዳደር እንዲኖረው የሆነበት ብዙ ምክነያቶች ይዘረዝራል፡፡ አዲስ አበባ ከሥያሜዋ ጀምሮ ሕገ ምንግስት ተብዬው ያጸደቀው ነው፡፡ አሁን ፊንፊኔ ምናምን ኦሮሞን ለማስደሰት ነው፡፡ የኢስ አባባ መንገዶችና ሰፈሮች እንደአስፈላጊነቱ በኦሮምኛ ይሰየማሉ ይላል፡፡ ይህም ያው ኦሮሞን ለመደለል ነው፡፡ በእንደእነዚህ ያ ነገሮች እንደሚረካ እናውቃለን ብለው ስለሚያስቡ፡፡ ሲጀምር የአዲስ አበባ መንደሮች የኦሮምኛን ሥያሜያቸውን አጥፍተውም አያውቁም፡፡ አሁንም ቢሆን ፒያሳና መርካቶን እንቀይር ካልተባለ የኦሮምኛ ሥያሜዎች እንዳሉ ናቸው፡፡ ከጊንፌሌ፣ ቀበና፣ የካ፣ ቦሌ፣ ጉለሌ፣ ምናም፡፡ እንግዲህ 7ኛ አብነት ምናምን የሚባሉትን ኦሮሞ እንደሚያስበው አማራ አልሰየማቸውም፡፡ ለቡ፣ አቃቂ፣ ቃሊቲ፣ ለመሆኑ ግን አማርኛው የት ነው፡፡ ምን አልባት መገናኛ፡፡

ኮተቤም አማርኛ አደለም፡፡ መንገዶቹም አሁን ተሰይመው ያሉት በአብዛኛው በሌሎች ሕዝቦች ነው፡፡ መቼም ኦሮሞ ነፍጠኛ የሚላቸው አንዱንም መንገድ በሥማቸው አልሰየሙም፡፡ እንዲህ ነው በኦሮሞ ላይ እየተሰራ ያለው ድራማ፡፡ ኦሮሞ በዚህ ከቀጠለ በቁጥርም አናሳ እንደሚሆን ይሰማኛል፡፡ በአለፉት 26 ዓመት ከምንም ነገር ውስጥ እንዳይታይ ተደርጎ በፖለቲካ ውዥንብር ውስጥ ከሌሎች ጋር እንዲቃርን ሲደረግ ነው የኖረው፡፡ አሁንም ብዙው አልነቃም፡፡

ሰሞኑን አቶ ለማንና ቡድናቸውን የሚያወድስ ጽሁፍ ጽፌ ነበር፡፡ እርግጥ ትንሽ ማየት እንዳለብን ተናግሬም ነበር፡፡ እስከዛሬ እየመጡበት በአለው ነበር ለገመግም የሞከርኩት፡፡ በዚች በአዲስ አበባዋ አዋጅ ዋና ጮቤ ረጋጭ እንደሆኑ ሳይ

ግን እስካሁንም ለካ ሕዝብን በእነሱ ቀለበት ውስጥ ለመክተት ነው የሚል ጥርጣሬ አደረብኝ፡፡ ከጥርጣሬም በላይ እነለማ የኦሮሞን ሕዝብ ለቀጣይ አመታት ለሽያጭ እንዳቀረቡት ተሰማኝ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ይህ አዋጅ ዛሬ መምጣቱ ብቻ ሳይሆን አዋጁን ራሳቸው እንደሚፈልጉት አዘጋጅተው የተወሰነ በተለያዩ ሚዲያዎች ሕዝብ ምን ይላል የሚለውን ለማወቅ ሲለቁና አይ እኛ አናውቀውም ሲሉ ከርመው ያው አሁን ያወጁት በዛ መሠረት ነበር፡፡ እነ ለማ አሳምረው ያውቁ ነበር፡፡ በሕግም በሞራልም፣ በምንም ዋስትና የሌለውን አዋጅ በኦሮሞ ሕዝብ ሥም አውጀው እነሱ ዋጋ ተቀበሉበት፡፡ በዚህ አዝናለሁ፡፡ አቶ ለማን መስሎኝ መጀመሪያ ሥራዎ የታሰሩ የሕዝብ ልጆች እንዲለቀቁ ማድረግ ነው የሚል ምክርም ሞከሬ ነበር፡፡ ለነገሩ ብዙ ሌሎች የኦሮሞ ልጆችም አቶ ለማን በዚህ ጉዳይ ትኩረት እንዲሰጡ መክረዋል፡፡ አሁን ግን ሳይ ገና የተናገሩት እንኳን ከሰው ጆሮ ገብቶ ሳይደመጥ የኦሮሞን ሕዝብ የገበያ ማቅረባቸው አሳዝኖኛል፡፡ እንደእኔ ይህን አዋጅ የአቶ ለማ ቡድን መቀበል አልነበረበትም ብቻ ሳይሆን በዚህ ወቅት ምንም አይነት ነገር በዚህ ጉዳይ ላይ ተባባሪ መሆን አልነበረበትም፡፡ ይህ 23 ዓመት ሥራ ላይ ያልዋለ አዋጅ ዛሬ ሕዝቡ ፍጹም ከዚህ የተለየ ጥያቄ እየጠየቀ በአለበት ወቅት ነው ለማ የ 23 ዓመት ሻጋታ ሕዝብ ትዝ የማይለውን ጉዳይ ያነሱት፡፡ እሱም የኦሮሞን ሕዝብ ጥያቄ ለለስኩልህና አርፈህ ተቀመጥ ለማለት፡፡

በአጠቃላይ የኦሮሞ ሕዝብ ወደነበረበት ማንነቱ ከአልተመለሰ እንዲሁ ይቀጥላል፡፡ አሁን አማራውንም እንደኦሮሞው ከታሪክና ማንነት ለማምከን ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ ኦሮሞን በተሳካ ሁኔታ እንዳመከኑት የተረዱት አሁን አማራውን ብሄረተኛ በሚል እያጦዙት ነው፡፡ ልብ በሉ በወያኔ የዘወር የነበረው የኦነግን እንቅስቃሴ ኢትዮጵያን በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ ሲኦል ማድረግ ነበር፡፡ 26 ዓመት ሕዝቡን ከኢትዮጵያዊነቱ አመከነው፡፡ ጀግኖች አባቶቹን አስጣለው ዛሬ ወኔ የሌለውና አላቃሻ አናሳ ከሚባሉትም በታች አቅም የሌለው ሆነ፡፡ ለዘመናት እየተገደለም እየታሰረም ቢሆን አማራ የተባለው ወያኔን ሲፈታተናት ነበር፡፡ ይህም ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚለው እምነቱ ጽኑ በሙኖሩ ነው፡፡ አሁን ወያኔ ኦሮሞን እንዴት እንዳመከነችው የሰራላትን ሥልት በአማራው ላይ በከፍተኛ ትኩረት እየሰራችበት ነው፡፡ ዛሬ አማራ የሚባለው እንደ አሸን የበዙ ድርጅቶች አሉት ሁሉም ይነታረካሉ፡፡ ብዙ ትውልድ ቤተ አማራ የተባለ የወያኔ ተላላኪ ተከታይ ሆኖ ገደል እየገባ ነው፡፡ አማራ በአማራነቱ አደለም ታሪክ ያለው፡፡ በኢትዮጵያዊነቱ እንጂ፡፡ ኢትዮጵያዊነት ከሌለ ጉልበት፣ ወኔ፣ ኣላማ የለም፡፡ አማራ በጊዜ ከአልነቃ በኦሮሞ የሆነው መምከን እንደሚመጣበት አትጠራጠሩ፡፡ ዛሬ ኦሮሞ የሰፈረበት ምድር የሌሎች ሆኖ ቢሆን ወያኔ አዲስ አበባ ላይ አደለም ደደቢት ቦታ ባልኖራት፡፡ አማራን ነፍጠኛ ሲሉት ያጣጣሉት መስሏቸው ነበር፡፡ ግን አዎ ነፍጠኛ ነኝ እኮራለሁ በዚህ ሲል ጭራሽ ወኔና ጉልበት እንደሆነው ገብቷቸዋል፡፡ አሁን የሚያዋጣው አማራን ተበዳይ ነህ በሚል የበታችነት ስሜት እንዲኖረው ማድረግና እንደኦሮሞ ከታሪክም፣ ከወኔም ማምከን ነው፡፡ ኦሮሞም ተጨቁነህል እየተባለ ነው የክብር ታሪኩንና ጀግኖች አባቶቹን ጥሎ ዛሬ ከምንም የሌለ መካን የሆነው፡፡ አንዴ ከታሪክና ከማንነቱ ከወጣላቸው የሚያደርጉትን እነሱ ያውቃሉ፡፡ ቤተ አማራ አማራውን ከታሪክና ከማንነት ለማምከን ኦነግ የተባለው የኦሮሞ ኮፒ በአማራ እንደሆነ ሰው ልብ ሊል ይገባዋል፡፡ ኦሮሞን ይሄው ዛሬ መላውን ኦሮሚያን ነጠቀውት አዲስ አባባንም ሰጠንህ ሲሉት እየተደሰተ ነው፡፡ ጊዜ በአገኙ ቁጥር ከቁጥሩም ያሳንሱታል፡፡ እነሱ በአዲስ አበባ ብቻ አደለም በሌላውም ዋና ዋና የኦሮሞ ግዛቶች ይስፋፋሉ፡፡

አመሰግናለሁ

ልዑል እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይጠብቅ!

አሜን!

ሰርጸ ደስታ